# የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭትን ለመከላከል ተከታታይ ግንዛቤ ሊፈጠር ይገባል ተባለ፡፡

አዲስ አበባ፣ ግንቦት 19/09/2015 ዓ.ም፤ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በስራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከልና አሁናዊ እውነታዎች በሚል ርዕስ ከ17 እስከ 19/09/2015 ዓ.ም ለ3 ተከታታይ ቀናት ለሰራተኞቹ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጠ፡፡

ስልጠናውን የሰጡት አቶ አንዱዓለም ግርማ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በአሁኑ ሰዓት በማህበረሰቡ ዘንድ መዘናጋትን በመፈጠሩ በአምራቹ ኃይል ላይ ጉዳት እያደረሰ ነው፡፡ ይህንን መከላከልና መቆጣጠር የሚቻለው ማህበረሰቡን በማስተማር እንዲሁም በስራ ቦታ ከሰራተኛው ጋር ቤተሰባዊ ግንኙነት በመፍጠርና በመወያየት ነው ሲለ ተናግረዋል፡፡

አያይዘውም በስራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከልና አሁናዊ እውነታዎችን በሚመለከት አቶ አንዱዓለም እንደገለፁት በሀገር አቀፍ ደረጃና በክልሎች ያለው የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት እየጨመረ መምጣቱንና ነገ የማይባል ጉዳይ በመሆኑ ሁላችንም ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል ብለዋል፡፡

የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለሰራተኛው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ሊሰጡ ይገባል፡፡መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን ሁሉም ሰው ግንዛቤ አለው በተግባር ማዋል ነው ችግር እየፈጠረ ያለው ብዙ እህት ወንድሞቻች እያጣን ነው፤ህፃናት ያላሳዳጊ አረጋዉያን ያለ ጧሪ እየቀሩ ነው፤ተከታታይ የሆነ ግንዛቤ ሊፈጠት ይገባል ሲሉ በስልጠናው የተሳተፉ ሰራተኞች ተናግረዋል፡፡



አቶ አንዱዓለም ግርማ በስራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከልና አሁናዊ እውነታዎች ላይ ስልጠና ሲሰጡ



የኮሚሽኑ ሰራተኞች ስልጠናውን ሲከታተሉ